# የድህረ ገፅ - ፕሮግራም ማመልከቻ መግለጫ

ለታዳጊ መሪዎች ፕሮግራም ያመልክቱ፦ የምሥራቅ አፍሪካ እትም

---

የዉሜን ዴሊቨር (Women Deliver) ታዳጊ መሪዎች ፕሮግራም [የኪስዋሂሊ እትም][የፈረንሳይኛ እትም] [የኪንያሩዋንዳ እትም] በከፍተኛ ስሜት የሚንቀሳቀሱ ወጣት አንቂዎችን በሃብት፣ በመድረክ፣ ግንኙነቶችን በመፍጠር፣ እና የሙግት ግቦቻቸውን የሚያጎሉ አስፈላጊ የሆኑ ስልጠናዎችን በመስጠት የሚደግፍ የሁለት አመት የአመራር ፕሮግራም ነው። ዉሜን ዴሊቨር (Women Deliver) ለጾታ እኩልነት እና ለጾታ እና ሥነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች (SRHR) ባለው ጠንካራ መሰጠት ወጣቶችን በእኩልነት የማሳተፍ እና አብሮ የመምራት ጠንካራ ታሪክም ያለው ነው።

የታዳጊ መሪዎች ፕሮግራም የእያንዳንዱን ታዳጊ መሪ የሙግት ጉዞ አብሮ የሚፈጥር ትኩረት ያለው አቅም ያለው በተወሰነ ርዕስ ላይ የሚያጠነጥን ፕሮግራም ነው። የእኛ ውጤት ነው፦

- የአስር አመት ልምዶችን በማገናዘብ የተገኘ
- እንደ ድርጅት የራሳችን ለውጦች ላይ በማተኮር የተገኘ
- በዘርፉ ካሉ ወጣቶች እና አጋሮች ጋር ብዙ ምክክሮችን በማከናወን የተገኘ

ዉሜን ዴሊቨር (Women Deliver) ተለዋዋጭ ፈንድ ማሰባሰብ፣ ድጋፍ፣ ስልጠናዎች እና ሃብቶች አስመልክቶ የሚያደርጉትን ጉዞ በማዘጋጀት ከእያንዳንዱ ታዳጊ መሪ ጋር አብሮ ይሰራል።

ማነው ለፕሮግራሙ ብቁ የሚሆነው?

እድሜያቸው (ከ15 እስከ 29) የሆኑ እና ማናቸውም ጾታ እና የጾታ ዝንባሌ ያላቸው እና

- ቡሩንዲ፣ ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ሩዋንዳ፣ ታንዛኒያ እና ዩጋንዳ የሚኖሩ እና የሚሰሩ
- ለጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች (SRHR) እና/ወይም ለጾታ እኩልነት የሚሟገቱ፣ በተለይ በማህበረሰባቸው ውስጥ የሚገኙ ወጣት ልጃገረዶችን በሚመለከት የሚሟገቱ። ቅድሚያ የሚሰጠው በእኛ የትኩረት ጉዳዮች አቅጣጫ፡ ዓለም አቀፋዊ የጤና ሽፋን፣ የአየር ንብረት ፍትህ እና የጸረ መብቶች እንቅስቃሴን መጋፈጥ ላይ ፍላጎት እና ልምድ ላላቸው ይሆናል።

[ዛሬ ታዳጊ መሪ ለመሆን ያመልክቱ ]

ማመልከቻዎች ሜይ **30 2024 11፡ 59 pm (23:59)** የምስራቅ አፍሪካ ሰዓት ላይ ያበቃሉ።

የማመልከቻ መመሪያ፦ ይህን ማመልከቻ ሲሞሉ የማመልከቻውን መመሪያ ማመልከቻውን ከመጀመርዎ በፊት እንዲያነቡት አጥብቀን እንመክራለን። ይህም በማመልከቻው ውስጥ ያሉትን ጥያቄዎች ቀድመው እንዲመለከቱ ያስችልዎታል እንዲሁም የማመልከቻውን ሂደት እና የምርጫ መስፈርቶችን አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ ይሰጥዎታል። ምላሾችዎን ከመስመር ውጭ አስቀድመው ማዘጋጀት ይችላሉ እንዲሁም የማመልከቻውን ሂደት መስመር ላይ አስቀምጠው በኋላ ተመልሰው ሞልተው ማስረከብ ይችላሉ።

የፕሮግራም አቅርቦቶች፦

በታዳጊ መሪዎች ፕሮግራም ውስጥ ያለ የእያንዳንዱ ታዳጊ መሪ ጉዞ በሙግት ግቦቻቸው መሰረት እንዲሁም የግል ክህሎታቸውን ለመገንባት እና እንደ ተሟጋች የማደግ የራሳቸው ግቦች ላይ በመመስረት የሚበጁ ይሆናል። በዚህ ጉዞ ውስጥ ለታዳጊ መሪዎች የሚሆኑ እድሎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

- ሥልጠና፣ ምክር እና የአቻ ትምህርት፦ ታዳጊ መሪዎችን በአስፈላጊ የሙግት ክህሎቶች እና እንደተሟጋች በሚኖራቸው ሚና ወሳኝ የሆኑ እውቀቶችን የማሳደግ አላማን ይዞ ታዳጊ መሪዎች ፕሮግራም ልዩ የሆነ በትብብር የመማማር ልምዶችን ያዘጋጃል። በተስተካከሉ፣ በራሳቸው በተፈጠሩ የመማሪያ ጉዞዎች ላይ በመመስረት፣ ታዳጊ መሪዎች ስልጠና ይሰጣሉ እና ይቀበላሉ፣ በጋራ ይፈጥራሉ እና ግብዓቶችንም ይቀበላሉ፣ ተገቢ ከሆኑ በክልላቸው ወይም አገራቸው ውስጥ ከሚገኙ እና የአቻ ለአቻ የእውቀት መጋራት እድሎች ተደራሽ ከሆኑ የወጣት መሪ የቀድሞ አባላት የምክር አገልግሎቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ።
- ተለዋዋጭ ድጋፍ፦ ታዳጊ መሪዎች ተሟጋችነታቸውን ለመደገፍ እና ድርጅቶቻቸውን ለማጎልበት የቴክኒክ ድጋፍ እና ያሉበትን አውድ መሰረት ያደረገ የገንዘብ እና ቁሳቁስ ድጋፍን ጨምሮ ከ5,000 እስከ 50,000 ዶላር የሚደርሱ የ18 ወራት፣ ተለዋዋጭ እና ተረስት ፈንዶችን ያገኛሉ።
- ስብሰባዎች፦ ዉሜን ዴሊቨር (Women Deliver) በማሰባሰብ ሃይሉ በሚገባ ይታወቃል እና ይህ ወደ ታዳጊ መሪዎች ፕሮግራም ይሰፋል። እያንዳንዱ ታዳጊ መሪ ሙሉ በሙሉ በገንዘብ በተደገፈ አንድ የመክፈቻ አውደ ጥናት እና ሙሉ በሙሉ በገንዘብ በተደገፈ የመዝጊያ አውደ ጥናት ላይ ይሳተፋል፣ እያንዳንዳቸው ታዳጊ መሪዎች መካከል ግንኙነት ለመፍጠር እና በተስተካከሉ የመማር ግቦቻቸው ላይ በመመስረት ትምህርትን ለማላቅ የተነደፉ ናቸው። አውደ ጥናቶቹ በጋራ የሚፈጠሩ እና በታዳጊ መሪዎች የሚመሩ ይሆናሉ።
- የአጋሮች ደጋፊ ሥነምህዳር፦ የታዳጊ መሪዎች ፕሮግራም ታዳጊ መሪዎች ከሀገራዊ፣ ክልላዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ የተሟጋችነት ጥምረቶች ወይም ትስስሮች ጋር የሚኖራቸውን ተደራሽነት ወይም መተባበር እና የሴቶችን የጋራ እንክብካቤ፣ ድጋፍ እና ትብብርን ይጨምራል።
- በክልላዊ እና አለምአቀፍ የተሟጋችነት ቦታዎች ላይ የፖለቲካ ተሳትፎ እና ተጽእኖ፦ እንደ የተሟጋችነት እቅዳቸው፣ የፖለቲካ ተሳትፎ እና ተጽዕኖ ፈጣሪ እድሎች በታዳጊ መሪዎች ተለይተው ታዳጊ መሪዎች ከውሳኔ ሰጪዎች እና ፖሊሲ አውጪዎች ጋር በቀጥታ እንዲገናኙ ያስችላቸዋል። እነዚህ ሙሉ የገንዘብ ድጋፍ የተደረገላቸው እድሎች አመራርን ወይም ተሟጋች አካልን መቀላቀል፣ በሚመለከታቸው ዝግጅቶች እና ስብሰባዎች ላይ መናገር ወይም በፖሊሲ ተሟጋችነት ስብሰባዎች እና መድረኮች ላይ መሳተፍን ሊያካትቱ ይችላሉ። ታዳጊ መሪዎች የራሳቸውን ግንኙነት ተጠቅመው ለተሟጋቾች የውሳኔ ሰጭ ሚናዎችን እና ቦታዎች ላይ እንዲደርሱ በሚያደርጉት የዉሜን ዴሊቨር (Women Deliver) ድጋፍ እንደ ባለሙያ እና መሪ መገለጫቸውን ይገነባሉ። በተጨማሪም፣ ዉሜን ዴሊቨር (Women Deliver) በዓለም አቀፋዊ ቦታዎች ላይ ፍትሃዊ እና ትርጉም ያለው ወጣቶችን በአለም አቀፍ እና ክልላዊ የውሳኔ ሰጭ ቦታዎች እንዲሳተፉ ግፊት በማድረግ የራሱን ተጽእኖ ያሳድጋል።

---

ብቁነት፡

- መገኛ ስፍራ፦ ዉሜን ዴሊቨር (Women Deliver) ታዳጊ መሪዎች ፕሮግራም የመጀመሪያው ክልል ምስራቅ አፍሪካ እንደሚሆን ሲገልፅ በጣም ደስ ብሎታል በተለይም በሚከተሉት አገሮች ውስጥ የሚኖሩ እና የሚሰሩ ወጣቶች፡ ብሩንዲ፣ ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ሩዋንዳ፣ ታንዛኒያ እና ኡጋንዳ
    - የእነዚህ አገሮች ዜጋ መሆን ወይም ከእነዚህ አገሮች የተገኙ መሆን አያስፈልገዎትም - በእነዚህ አገሮች ውስጥ መኖር እና ተሟጋችነትዎን መምራት ብቻ ያስፈልግዎታል።

- o ልዩ መስፈርቶች፦ ከእነዚህ አገሮች ውስጥ በአንዱ ካልኖሩ (ነገር ግን የተሚጋችነት ሥራዎ አሁንም ከእነዚህ አገሮች አንዱ ላይ ያነጣጠረ ከሆነ) ምክንያቱም የተሚጋችነት ሥራዎን እያከናወኑ በዛ መኖር ለደህንነትዎ አስተማማኝ ስላልሆነ፣ ለዚህ ፕሮግራም ብቁ ነዎት። ጉዳዩ ይህ ከሆነ በማመልከቻው ውስጥ ስላለዎት ሁኔታ ለማብራራት እድሉ ይሰጥዎታል።
  - ▪ ምሳሌ፦ እርስዎ ብቁ ከሆኑ አገሮች በአንዱ የLGBTQIA+ መብቶች ተሚጋች ነዎት፣ ነገር ግን ይህንን ስራ በሚሰሩበት ጊዜ በብቁ አገር ውስጥ መኖር ለእርስዎ አስተማማኝ ስላልሆነ በደቡብ አፍሪካ እየኖሩ ነው።
- ● ዕድሜ፦ ለዚህ ፕሮግራም የሚያመለክቱ፦ ከኦክቶበር 1፣ 2024 በኋላ ሲሰላ ዕድሚያቸው ከ15-29 መካከል መሆን አለበት። ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ፣ ወደዚህ ፕሮግራም ለመቀላቀል ከወላጅ/አሳዳጊ ፈቃድ እና ስምምነት ያስፈልግዎታል።
- ● ፆታ / ሥርዓተ ፆታ፦ ይህ ፕሮግራም ለሁሉም እና ፆታ እና ፆታዊ ማንነቶች በተለይም ደግሞ እራሳቸውን እንደ ልጃገረዶች፣ እና ሴቶች አድርገው ለለዩ ክፍት ነው።
- ● ተሚጋችነት፦ ለጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች (SRHR) እና/ወይም ለጾታ እኩልነት የሚመሚገቱ፣ በተለይ በማህበረሰባቸው ውስጥ የሚገኙ ወጣት ልጃገረዶችን በሚመለከት የሚሚገቱ መሆን አለበት። ቅድሚያ የሚሰጠው በእኛ የትኩረት ጉዳዮች አቅጣጫ፡ ዓለም አቀፋዊ የጤና ሽፋን፣ የየአየር ንብረት ፍትህ እና የጸረ መብቶች እንቅስቃሴን መጋፈጥ ላይ ፍላጎት እና ልምድ ላላቸው ይሆናል።
  - o [ዓለም አቀፋዊ የጤና ሽፋን](): ዓለም አቀፋዊ የጤና ሽፋን ማለት ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት የገንዘብ ጫና ሳይኖር ለሁሉም ሰው ተደራሽ ናቸው ማለት ነው ። ዓለም አቀፋዊ የጤና ሽፋን የተለያዩ የጤና አገልግሎቶችን የሚያጠቃልል ቢሆንም፣ዓለም አቀፋዊ የጤና ሽፋን እና የጤና እንክብካቤን ለሁሉም እውን ለማድረግ ለልጃገረዶች እና ለሴቶች የጤና ፍላጎቶች በተለይም ለጾታዊ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች (SRHR) ቅድሚያ መስጠት ወሳኝ ነው።
  - o [የአየር ንብረት ፍትህ]()፦ አለም አቀፍ የአየር ንብረት ቀውስ በትንሹ አስተዋጽዖ ያደረጉትን፡ በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጃገረዶችን፣ ሴቶችን እና የተለያየ የስርዓተ ጾታ ሁኔታ ያላቸውን ሰዎች ባልተመጣጠነ ሁኔታ ይጎዳል። የአየር ንብረት አስደንጋጭ ክስተቶች እና ውጥረቶችን ለመቋቋም እና ለማገገም አነስተኛ አቅም አላቸው። እንዲሁም አብዛኛውን ሸክሙን በማህበረሰብ እና ቤተሰብ የመቋቋሚያ ስልቶች ይሸከሙታል።
  - o [የፀረ-መብት እንቅስቃሴን መቃወም]()፦ ለበርካታ አስርት ዓመታት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ኃይለኛ እና ጥሩ የገንዘብ ድጋፍ ያለው የፀረ-መብት ተዋናዮች ጥምረት የልጃገረዶችን እና የሴቶችን በሰውነታቸው ላይ የማዘዝን እና የጾታ እና የስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶችን (SRHR) ያለማቋረጥ ለመገዳደር እና ለመሸርሸር ሞክሯል። ፀረ-ጾታ እንቅስቃሴን ለመደገፍ ቢያንስ 1 ቢሊዮን ዶላር በዓለም ዙሪያ ተላልፏል። ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣው ተጽእኖዋቸው በአገር አቀፍ ደረጃ በተለያዩ የተሃድሶ ፖሊሲዎች ውስጥ በግልጽ ይታያል። በሲቪል ማህበረሰብ ውስጥ የሰብአዊ መብት ቋንቋን ለመጠቀም እና መሳሪያ ለማድረግ እና ለጾታ እና የስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶችን (SRHR) ደጋፊ የሆኑ ድምፆችን ለማፈን በአለም አቀፍ ደረጃ ስልታዊ መድረኮችን አስርገዋል።
- ● [የሥነምግባር ደንብ]()፦ ይህንን ፕሮግራም ለመቀላቀል ከድርጅታችን የስነ ምግባር ደንብ ጋር መስማማት አለብዎት. በተጨማሪም፣ ሁሉም ታዳጊ መሪዎች ጥበቃ ይደረግላቸዋል እና ከዉሜን ዴሊቨር (Women Deliver) የልጆች እና ወጣት ከአደጋ ጥበቃ ፖሊሲ ጋር መስማማት አለባቸው [የኪስዋሂሊ እትም] [የፈረንሳይኛ እትም] [ኪንያሩዋንዳ እትም]።
- ● ቋንቋ፡ ይህ ፕሮግራም የእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቃትን ይጠይቃል። የፕሮግራሙን የወደፊት ደግግሞ ወደ በዙ ቋንቋዎች ለማስፋት እየሰራን ነው። ስለዚህ ፕሮግራም ከቤተሰብዎ ወይም ከማህበረሰብዎ ጋር እንግሊዝኛ ለማይችሉ ማካፈል ከፈለጉ ሰነዶችን ወደ አማርኛ ተርጉመናል።
  - o ድረገጽ፦ [ታዳጊ መሪዎች ለለውጥ]()
  - o ታዳጊ መሪዎች ፕሮግራም [የሥነምግባር ደንብ]()
  - o የዉሜን ዴሊቨር (Women Deliver) [የልጆች እና ወጣት ከአደጋ ጥበቃ ፖሊሲ]()

- የበይነመረብ ግንኙነት፦ የፕሮግራም እንቅስቃሴዎች በዋናነት በመስመር ላይ ይከናወናሉ፣ ነገር ግን አንዳንድ ተግባራት ለምሳሌ የመክፈቻ እና የመዝጊያ አውደ ጥናቶች በአካል በመገኘት ይከናወናሉ። ዉሜን ዴሊቨር (Women Deliver) ታዳጊ መሪዎችን ለፕሮግራም ተግባራት በይነመረብን እንዲደርሱ የመረጃ እና/ወይም የሃርድዌር አበል ክፍያ በማቅረቡ ደስተኛ ነው።
- ንቁ ተሳትፎ፦ ከዚህ ፕሮግራም ከፍተኛውን ጥቅም ለማግኘት ታዳጊ መሪዎች በፕሮግራም አቅርቦቶች ላይ በንቃት ለመሳተፍ ጽኑ እና ስሜታዊ ተሟጋቾች መሆን እና ለራሳቸው የሙግት ፕሮጀክቶች ትልቅ ጊዜ ለመስጠት ፍላጎት ማሳየት አለባቸው። ይህ ለእርስዎ ምን እንደሚመስል ለበለጠ መረጃ፣ እባክዎ ይህንን [የተሳትፎ መመሪያ ይመልከቱ]

ስለብቁነትዎ ጥያቄዎች? ኢሜይል ELP-App@womendeliver.org

## የምልመላ ጊዜ

- **15** ኤፕሪል **2024**፦ ለ**2024** የታዳጊ መሪዎች ፕሮግራም ማመልከቻ፦ የምስራቅ አፍሪካ እትም 12:00 am በየምስራቅ አፍሪካ ሰዓት (ኢ.ኤቲ) ይከፈታል።
- ከኤፕሪል **– ሜይ 2024**፦ ዉሜን ዴሊቨር (Women Deliver) በታዳጊ መሪዎች ፕሮግራም ላይ ሁለት የመረጃ ክፍለ ጊዜዎችን ያስተናግዳል። ለመቀላቀል ፍላጎት ካለዎት ከታች መመዝገብ ይችላሉ። መገኘት ካልቻሉ አሁንም ለአንዱ መመዝገብ ይችላሉ እና የተቀዳው ቅጂ ወደ መለያዎ ይላካል።
    - o **29** ኤፕሪል ከ**4:00 – 6:00 pm** ኢ.ኤቲ (እዚህ ይመዝገቡ)
    - o **15** ሜይ ከ**4:00 – 6:00 pm** ኢ.ኤቲ ( እዚህይመዝገቡ)
- **30** ሜይ **2024**፦ ለ**2024** የምስራቅ አፍሪካ ታዳጊ መሪዎች ቡድን ማመልከቻ 11:59 PM (23:59) የምስራቅ አፍሪካ ሰዓት ላይ ይዘጋል። ማመልከቻ ጊዜው ከመጠናቀቁ ከሶስት ቀናት በፊት ማሳሰቢያ እንዲደርስዎት እዚህ ጠቅ ያድርጉ።
- ከጁን **–** ጁላይ **2024**፦ ማመልከቻዎች ከዉሜን ዴሊቨር (Women Deliver) ሰራተኞች፣ በተውጣጡ የወጣት መሪዎች የቀድሞ አባላት እና ጥልቅ ክልላዊ እና የጉዳይ-አካባቢ እውቀት ባላቸው አጋር ድርጅቶች በተካተቱ የተለያዩ መራጭ ኮሚቴዎች ይገመገማሉ። ከቀረቡት ማመልከቻዎች ሁሉ በግምት 60 የሚሆኑ የግማሽ ፍፃሜ ተወዳዳሪዎች ለቀጣዩ ዙር ይመረጣሉ።
- ጁላይ **2024** መጨረሻ፦ ሁሉም አመልካቾች ለግማሽ ፍጻሜ ተወዳዳሪ ከተመረጡ ወይም ካልተመረጡ ማሳወቂያ ይደርሳቸዋል። ለግማሽ ፍጻሜ አልፈው ከተመረጡ፣ ለማመልከቻ ሂደቱ የመጨረሻ ደረጃ ለሆነው የቡድን ቃለ መጠይቅ እራስዎን እንዲያዘጋጁ ይጋበዛሉ።
- ኦገስት **2024**፦ የቡድን ቃለ መጠይቆች ለግማሽ ፍጻሜ ካለፉት ጋር ይካሄዳሉ።
- ኦገስት **2024** መጨረሻ፦ የመጨረሻ ምርጫዎች ይደረጋሉ፣ እና ሁሉም የግማሽ ፍፃሜ ተወዳዳሪዎች ከተመረጡ ወይም ካልተመረጡ ማሳወቂያ ይደርሳቸዋል።
- ሴፕቴምበር **2024**፦ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክትን ጨምሮ የታዳጊ መሪዎችን መቀበል ይጀመራል። ታዳጊ መሪዎች አዲሱን የታዳጊ መሪዎች ቡድን ለማስተዋወቅ የሚያገለግሉ እና ወደ ዉሜን ዴሊቨር (Women Deliver) ድር ጣቢያ የሚታከሉ መረጃዎችን እንዲያካፍሉ ይጠየቃሉ።
- ኦክቶበር **1**፣ **2024**፦ የታዳጊ ወጣቶች ለለውጥ ፕሮግራም በይፋ ይጀመራል

ስለ ታዳጊ መሪዎች ፕሮግራም፦

- የፕሮግራሙ ግቦች፦
  - ከጾታ እና የስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች **(SRHR)** ጋር የተያያዙ የራሳቸውን የሙግት ፕሮጀክቶች ለማዳበር እና ለመተግበር የሚያስችሉ በተለይም በጉርምስና ዕድሜ ላይ ለሚገኙ ልጃገረዶች ያሉበትን አውድ ያገናዘቡ የታዳጊ መሪዎች፣ የጎለበቱ ክህሎቶች የተገነቡ ብራንዶች እና የተሻሻሉ አቅሞች ።
  - በፖለቲካዊ እና ፋይናንሺያል ፖሊሲዎች ላይ ተጽእኖ መፍጠር በሚችሉ እንደ ታዳጊ መሪዎች እና ውሳኔ ሰጪዎች ባሉ በተለምዶ ችላ በተባሉ ድምፆች መካከል ያሉ ግንኙነቶችን አጠናክሯል።
  - በታዳጊ መሪዎች እና ውሳኔ ሰጪዎች መካከል ድልድዮችን ለመገንባት እና ጠንካራ አጋርነት ለማዳበር በማይመስሉ አጋሮች መካከል ዓለም አቀፍ የግንኙነት እድሎችን ጨምሯል።
  - የጾታ እና የስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶችን (SRHR) በአካባቢያቸው እና በአገራዊ ሁኔታቸው እና በዓለም አቀፍ ቦታዎች ላይ ለማራመድ እና ውሳኔ ሰጪዎችን ተጠያቂ ለማድረግ የሚያስችል የታዳጊ መሪዎች፣ የታዳጊ መሪ የቀድሞ አባላት እና የወጣቶች ተሚጋቾች እንቅስቃሴ።
- በዙር የሚደርስ ክልላዊ ሞዴል ፦ ዉሜን ዴሊቨር (Women Deliver) በአንድ ጊዜ በአንድ ክልል ላይ ያተኩራል፣ ይህም ከክልሉ ለሚመጡ ታዳጊ መሪዎች የተደራጀ፣ አውድ-ተኮር ድጋፍ እና የአካባቢ እውቀትን ይሰጣል። ቡድኑ ከተነሳ እና መስራት ከጀመረ፣ ዉሜን ዴሊቨር (Women Deliver) ለሌላ ክልል ምልመላ ይጀምራል። በክልሎች ላይ በአንድ ጊዜ የማተኮር አላማ ከክልሉ በመጡ ታዳጊ አመራሮች መካከል የማህበረሰብ፣ የእርስ በርስ ትስስር እና የትብብር ግንባታ ስሜት መፍጠር እና ማጎልበት ነው።
- የተደራጀ ድጋፍ፦ ለእያንዳንዱ ታዳጊ መሪ ጠንከር ያለ የግለሰብ ድጋፍ ለመስጠት፣ የእያንዳንዱ ክልል የስብስብ መጠኖች ከ30-50 ግለሰቦች በትብብር ለመስራት እድል ይኖራቸዋል። ይህም እያንዳንዱ ግለሰብ ተሚጋችነታቸውን በብቃት ለመተግበር የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ እንደሚያገኝ ያረጋግጣል።
- በጉርምስና እድሜ ላይ የሚገኙ ልጃገረዶች የታደሰ ትኩረት ፦ የልጃገረዶች የጉርምስና ወቅት ጅማሬ በሰውነታቸው ላይ የማዘዝን መብት መገደብ፣ መጠየቅ እና መቆጣጠር የተለያዩ እይታዎችን ይወክላል። ይህንን የልዩነት ነጥብ ኢላማ በማድረግ - እና ለዚህ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ምክንያቶች - ታዳጊ መሪዎች ጉዳዩን በዚህ የመለወጫ ነጥብ ለመፍታት ይሠራሉ።
- ችግር ላለባቸው አካባቢዎች የተሻለ ሌንስ ማቅረብ ፦ የታዳጊ መሪዎች ስራ በጾታ እና ሥነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች(SRHR) እና የጾታ እኩልነት ላይ በሰፊው የሚያተኩር ከሆን በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥን ይሆናል፡ የአየር ንብረት ፍትህ፣ ጸረ መብቶችን እንቅስቃሴዎችን መቃወም እና ዓለም አቀፋዊ የጤና ሽፋን።
- በማእከል የሚደረግ የአእምሮ ጤንነት፣ ደህንነት እና ከአደጋ ጥበቃ የተሚጋቾች እና የአንቂዎች ስራ በፍጹም አያልቅም እንዲሁም ዋጋ የሚያስከፍል ሆኖ ሊመጣ ይችላል። ዉሜን ዴሊቨር (Women Deliver) በእያንዳንዱ የጉዟቸው ደረጃ መታገዛቸውን በማረጋገጥ የመሪዎችን የአእምሮ እና የስሜት ጤንነት ይደግፋል።